# አገልግሎት ቁ1 (8)

በየትኛውም ዘመን ውስጥ ምንም ዓይነት ጠንካራና የተከናወነላት ብለን የምናስባት ቤተ ክርስትያን 100% ምዕመኖችዋ በሙሉ በአገልግሎት ተሳትፎ የሚያደርጉ ይሆናሉ ብሎ ማመን ያስቸግራል። ሆኖም በአብዛኛው አብያተ ክርስትያናት (የእኛንም ጨምሮ ማለት ነው) ከምዕ መናቸው ያልተቆጠበ ተሳትፎ የሚያሳዩት ቁጥር ምናልባት ቢበዛ ከ20% እንደማይበልጥ እገምታለሁ። ታዲያ ይህ አይነቱ ነገር የክርስቶስን አካል ለማነጽ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን መመሪያ የሚጻረር በመሆኑ ቅዱሳን ይህ ስህተት መሆኑን እንዲገነዘቡና እግዚአብሄር ወደ ሚጠብቅብን እውነት ለመምራት ይህ ትምህርት ተዘጋጅቷል።

ጥናቱ የተዘጋጀው ቅደም ተከተልን ይዞ ስለሆነ እንደ ቅደም ተከተሉ ቢጠና ጠቃሚ ነው ብለን እናምናለን። የመጀመሪያው ጥናት የሚያተኩረው አማኝ ሁሉ እንደማንኛውም ሰው በሰይጣን ባርነት ሥር እንደ ነበረ፣ ከነበረበት ሁኔታም ለመውጣት በራሱ ምንም መንገድ እንዳልነበረው ነገር ግን እግዚአብሄር ከዚያ ባርነት እንዳወጣው የሚያስተምር ነው። ከዚያ በመቀጠል ሁለተኛው ጥናት እግዚአብሄር ከባርነት ነፃ ሲያወጣው የራሱ ምክንያት እንደነበረውና ይህም ምክንያቱ አምልኮ/አገልግሎት እንደነበረ የሚያስተምረን ጥናት ነው። ሶስተኛው ጥናት ደግሞ እያንዳንዱ አማኝ ከባርነት ነጻ ያወጣውን እግዚአብሄርን እንዲያገለግል የሚያስችለው የጸጋ ስጦታ እንደተሰጠው የሚያስገነዝብ ነው። አራተኛው ጥናት ደግሞ የጸጋውን ሥጦታ ተቀብሎ ማገልገል ለአምኝ ግዴታው እንጂ ለምርጫ የተተወለት ነገር እንዳልሆነ የሚያስገነዝብ ሲሆን፤ አምስተኛው ጥናት አገልግሎትን ግዴታ ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው አካሉን ማሳደግ የተወሰኑ ሰዎችን ወይም የብዙዎችን ስዎች እንቅስቃሴ ብቻ ሳይሆን የቅዱሳኑን ሁሉ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነገር መሆኑን ያስታውሰናል። ስድስተኛውና የመጨረሻው ጥናት ደግሞ የጸጋውን ሥጦታ ብንቀበል፣ በተቀበልነው ጸጋም ብንጠቀምበትና ብናገለግል፤ ከምናደርገው ነገር አልፎ ልብን የሚፈትነውና ሃሳብን የሚመዝነውን ጌታ ስለምናገለግል እንዴትና በምን አይነት መንፈስ እንደምናገለግለው መጠንቀቅ እንደሚኖርብን የሚያስገነዝበንን ጥናት በማጥናት ጥናቱን እናገባድዳለን።

እነዚህን ጥናቶች ከማጥናታችን በፊትም ሆነ በማጥናት ላይ እያለን ጌታ መንፈስ ቅዱስ እውነቱን ለእያንዳንዳችን ህይወት እንዲገልጥ እኛም ደግሞ ለመታዘዝ ልባችን እንዲዘጋጅ በጸሎት ልንቀርብ ያስፈልጋል። ጌታ ይርዳን !!

# <u>ጥናት አንድ (ኤፌ 2፡1-10)</u>

***የጥናቱ ዓላማ፣ አማኝ ራሱን መርዳት በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ እያለ በእግዚአብሄር ጸጋ ብቻ ህይወትን እንዳገኘ በማሳየት ለምስጋና እንዲነቃቃ ለመርዳት።***

የምናሰላስለው ጥቅስ: «ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና ይህም የእግዚአብሄር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም::» ኤፌ 2:8-9

1. **ኤፌ 2፥1-10 በአንድነት ይነበብ።** ይህ ክፍል ስለ ቀድሞ ሁኔታችን የሚነግረንን ነገሮች ተናገር::
2. ***ቆመውና እየተራመዱ የሚፈልጉትን ሁሉ እያደረጉ ያሉትን ሰዎች ሙታን አድርጎ ስለማቅረቡ የአንተ ግንዛቤ ይህንን በተመለከተ ምንድነው?***
3. በቁ 3 ላይ «እኛ ሁላችን» «እንደ ሌሎቹም ደግሞ» የሚሉት ቃላት እግዚአብሄር ስለመረጣቸው ሰዎች አይነት የሚገልጹት እውነት ምንድነው?
4. **ቀድሞ ተገዢነታችን ለማን እንደነበረ ነው ይህ ክፍል የሚያረጋግጥልን?** በዚህ ክፍል መሰረት ይህ ሁኔታችን የተቀየረው መቼና በማን ነው?
5. **“በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ <u>ፈቃድ</u> በፊት ተመላለሳችሁባቸው።”** ሲል በኛ ላይ ስለነበረው ስልጣን ሁኔታ ምን ያሳይሃል? **ይህንን ሃሳብ በባሪያና በጌታ መሃል ካለው ግንኙነት ጋራ በማነጻጸር ተናገር።**
6. **እግዚአብሄር የነበርንበትን ሁኔታ ለመቀየር ያደረጋቸውን ነገሮች በዝርዝር ተናገር።**
7. **ዛሬ ከተነበበው ክፍል የእግዚአብሄርን ፍቅር ጥልቀት የሚገልጹት ሃሳቦች የትኞቹ ናቸው?**
8. «...በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን፡» ሲል ሃዋርያው ምን ማለቱ ነው? ስለ መፈጠራችንስ ምክንያት አድርጎ የሚያቀርበው ነገር ምንድነው?
9. ከነበርክበት ማጥ ውስጥ ለመውጣት መፍትሄው እግዚአብሄር ብቻ እንደነበረ ምን ያህል ገብቶሃል? ታዲያ በዚህ ነጻነትህ ጸንተህ ለመቆም ምን ያህል ቆርጠሃል? ምን ያህልስ ለምስጋና አነሳስቶሃል?

# ጥናት ሁለት (ዘጸ 8:1-15)

የጥናቱ ዓላማ:- አማኝ ከጠላት ባርነት ነፃ ከወጣበት ዓላማዎች አንዱና ዋነኛው እግዚአብሄርን ለማምለክና ለማገልገል እንደሆነ ለመማር::

የምናሰላስለው ጥቅስ: «እግዚአብሄር ሙሴን ተናገረው:- ወደ ፈርዖን ግባ እንዲህም በለው:- ያገለግለኝ/ያመልከኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ::» ዘጸ 8:1

1. እግዚአብሄር ሙሴ ለፈርዖን እንዲነግረው የሰጠው ትዕዛዝ ምን ነበረ? ለሙሴና ለአሮንስ እንዲያደርጉ ለራሳቸው የተሰጣቸው ትዕዛዝ ምን ነበረ?
2. በዘጸአት 8:1 እና በኤፌሶን 2:10 መካከል የምታየው ተመሳሳይነት ምንድነው?
3. በዚህ ክፍል መሰረት በፈርዖንና በህዝቡ ላይ የመጣባቸው መቅሰፍት ምክንያቱ ምን እንደነበር በአንድ ቃል ጨምቀህ ተናገር ብትባል ምን ትላለህ?
4. የመቅሰፍቱ መከሰትና እንደገና ደግሞ የመቅሰፍቱ መቆም በፈርዖን ህይወት ውስጥ ያስከተለው ሁኔታ ምን እንደነበረ አስረዳ::
5. በዚህ ዘመንስ ሰዎች ፊታቸውን ወደ እግዚአብሄር እንዲመልሱ ከሚያስገድዷቸው ሁኔታዎች ጥቂቶቹን ዘርዝር:: ሁኔታቸው ሲስተካከልስ በአብዛኛው ምን ለውጥ ይታያል?
6. በቁ 8-11 መሰረት ፈርዖን እንዲጸለይለት ሲጠይቅ፤ ከዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዲማር ሙሴ የፈለገው ዋነኛ ነገር ምን ነበረ?
7. ይህ ሙሴ ለፈርዖን ትምህርት እንዲሆነው የተናገረው ሃሳብ ለእኛስ በዚህ ዘመን ላለነው ስለ ተአምራትና ድንቅ ዋነኛ አላማ ምን ይጠቁመናል?
8. በመጨረሻ እግዚአብሄር እስራኤልን በተአምርና በድንቅ ከጠላቶቻቸው መንጋጋ እንዳስለቀቀ እናውቃለን:: የእነርሱንና የእኛን ነጻ አወጣጥ በማነጻጸር የሚመሳሰልበትንና የሚለያይበትን ሁኔታዎች ተናገር:: ከሁለቱ የትኛው የሚበልጥ ሆኖ ታየዋለህ? ለምን?
9. በዚህ ጥናት መሰረት እኛ ህዝቦቹ ነጻ የወጣንበት ምክንያት ለምንድነው? ተግባራችን ምን ያህል ይህንን እውነት ይገልጣል?

# ጥናት ሶስት (1ኛ ጴጥ 4፡7-11)

***የጥናቱ ዓላማ፡ እግዚአብሄር ለእያንዳንዱ አማኝ የጸጋን ስጦታ እንደሰጠ ለማሳየትና እያንዳንዱም በተሰጠው ስጦታ እንዲያገለግል ለማበረታታት።***

*የምናሰላስለው ጥቅስ: «እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በእርሳችሁ አገልግሉ፤» **1ኛ ጴጥ 4:10***

1. **1 ጴጥ 4፥7-11 በአንድነት** ይነበብ:: በክፍሉ *መሰረት* በቤተ **ክርስትያን** ውስጥ *የጸጋ ስጦታን የተቀበሉት እነማን ናቸው?*
2. *እኔ ስጦታ የለኝም የሚል አማኝ ገጥሞህ ያውቃል ወይ? በአንተ አመለካከት ለምንድነው በአማኞች ዘንድ የዚህ ዓይነቱ ከእውነት የራቀ ሃሳብ የሚስተናገደው?*
3. ***ስጦታው ስለተሰጠበት ምክንያት ክፍሉ የሚያስተምረን ምንድነው?** በዚህ ክፍል ሶስት ጊዜ የተጠቀሰና **ይህንን** እውነት አጉልቶ የሚያሳየው ቃል ምንድነው?*
4. ***ስጦታን እግዚአብሄር ከሰጠበት ዓላማ ውጭ ሰዎች ሲጠቀሙበት አይተህ ታውቃለህ ወይ? በምሳሌ አስረዳ።***
5. *የሚያገለግል ማንኛውም አማኝ ሊኖረው ስለሚገባው አመለካከትና አስተሳሰብ ይህ ክፍል የሚያስተምረን ምንድነው?*
6. *አገልግሎታችን ብዙ ዝግጅትና ብዙ ጊዜ ጠፍቶበት ለምንድነው አብዛኛውን ጊዜ ፍሬ አልባና ሃይል የሌለው ሆኖ የሚገኘው?*
7. *በጥያቄ ቁ 3 ላይ አገልግሎት የተሰጠበትን ምክንያት ተመልክተናል:: ይህ ምንባብ ስለ አገልግሎት ግብስ የሚነግረን እውነት ምንድነው?*
8. ***በግላችንም ሆነ እንደ ቤተ ክርስትያን አገልግሎት** ዋነኛ ግቡን እንዲስት ሊያድርጉ የሚችሉትን ዋና ዋና ምክንያቶች ምን ምንድናቸው?*
9. *እኛ እዚህ የምንገኘው ሁላችን ስጦታን እንደተቀበልን ከዛሬው ትምህርት ምን ያህል እርግጠኛ አደረገህ? የተለየ ለህይወትህ የተማርከውን እውነት ካለህ ለወገኖች አካፍል?*

# ጥናት አራት (ማቴ 25:14-30)

የጥናቱ ዓላማ:- ለአማኝ በተሰጠው የፀጋ ስጦታ በክርስቶስ አካል ውስጥ በአገልግሎት መሳተፍ ግዴታ እንጂ ምርጫ እንዳልሆነ ለማስገንዘብ፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ: «ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፤ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር፡፡» ማቴ 25:27

1. ማቴዎስ 25:14-30 በአንድነት ይነበብ፡፡ በዚህ ክፍል የጌታውን አሰጣጥ በተመለከተ ጎልቶ የሚታዩህን ነገሮችን ዘርዝር፡፡
2. በዚህ ክፍል ያነበብነው የመክሊት አሰጣጥ በ1ኛ ቆሮ 12:11 ከሰፈረው እውነት ጋራ የሚመሳሰለው በምን መንገድ ነው?
3. መክሊቱን የተቀበሉት ባሪያዎች እያንዳንዳቸው የጌታቸውን ስጦታ በምን ሁኔታ ነው የያዙት? ለምን?
4. በዘመናችን አንድ አማኝ መክሊቱን ቀበረ ወይም አተረፈበት ማለት ምን ማለት ነው? የተቀበለውን ስጦታ የሚቀብርባቸው አንዳንድ ምክንያቶች ዘርዝር፡፡
5. መክሊቱን የሰጠው ጌታ ለሁለቱ ላተረፉት ባሮችና መክሊቱን ለቀበረው ባርያ የተናገራቸውን ነገር አነጻጽር፡፡
6. ለምንድነው አምስት መክሊት ያተረፈው ሁለት ካተረፈው የተለየ ነገር ሲሰጠው የማይታየው? ከዚህ ልንማር የምንችለው ግልጽ የሆነ እውነት ምንድነው?
7. ቁ 21 ላይ «ጌታውም፤ መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃልሁ...» ይህ ምስጋና ከአገልጋይ ስለሚጠበቁ ነገሮች የሚያሳየን ምንድነው?
8. በተለይ ቁ 26 ትን ስናነብ መክሊቱን ያደለው ጌታ ከባሪያዎቹ የጠበቀው ነገር ምን ነበረ?
9. አማኝ ሁሉ ስጦታን ከመንፈስ ቀዱስ እንደተቀበለ በቀደመው ጥናት ተምረናል፡፡ ጌታ ዛሬ ቢገለጥ የሚያስመሰግንህ ወይስ የሚያስነቅፍህ ሁኔታ ላይ ነህ ያኸው? ለመለወጥ እድል ስላለህ ዛሬውኑ እርምጃ መውሰድ ትችላለህ

# ጥናት አምስት (ኤፌ 4፥11-16)

***የጥናቱ ዓላማ፡ የክርስቶስን አካል ማሳደግ የተወሰኑ ሰዎች ሃልፊነት ሳይሆን የእያንዳንዱ አማኝ ሃላፊነት እንደሆነ ለማስተማር።***

የምናሰላስለው ጥቅስ:«እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሰራ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተገጣጠመና እየተያያዘ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል፡፡» ኤፌ 4:16

1. ***ኤፌሶን 4፥11-16 ትን ስናነብ፣ አንድነት የሚገኝበትን መንገድ ይህ ክፍል እንዴት አድርጎ ነው የሚያቀርበው?***
2. ***ወደ አንድነት ሊያደርሱን የሚችሉትን ሁለት ነጥቦች በመዘርዘር እንዴትና በምን መንገድ ወደዚህ ነገር ሊያመጡን እንደሚችሉ አስረዳ። የተሰጡን አገልጋዮች አስተዋጽዖ በዚህ ረገድ ምን እንደሆነ ተናገር።***
3. ***አገልግሎት የሚካሄደው እስከመቼ ወይም ምን እስከሚሆን ድረስ ነው ይላል ክፍሉ?***
4. ***"የክርስቶስ ሙላቱ"የሚለውን በቁ 13 ላይ የሚገኘውን ሃሳብ የምትረዳው እንዴት ነው?***
5. ***"...በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ" ይህንን ማድረግ የሚኖርብን እንዴት ነው ይለናል ምንባቡ?***
6. ***እውነትና ፍቅርን አንድ ላይ ማራመድ የሚያዳግተው ለምን ይመስልሃል? እውነትን ያለ ፍቅር፣ ፍቅርን ደግሞ ያለ እውነት መያዝ ለክርስትና አደገኛነቱን አስረዳ።***
7. ***በዚህ ምንባብ መሠረት የክርስቶስን አካል ለማነጽና ለማሳደግ ሃላፊነት ያለው ማን ነው?***
8. ***የእያንዳንዱ ብልት በሚገባውን አስዋጽዖ ለአካሉ አለማበርከቱ የሚያስከትለው ጉዳት ያለ ይመስልሃል ወይ? ለምን?***
9. ***በክርስቶስ አካል ውስጥ አንተ እያደረከው ያለኸው አስተዋጽዖ አለ ወይ? የአንተ ሃላፊነትህን አለመወጣት ለአካሉ እንደሚገባ አለማደግ አስተዋጽዖ እያደረክ እንደሆነ ትረዳለህ ወይ?***

# ጥናት ስድስት (1 ቆሮ 3፥10-15)

***የጥናቱ ዓላማ፡ ጌታ አገልግሎታችንን መፈጸማችንን ብቻ ሳይሆን እንዴትና በምን ዓይነት መንፈስ እንደምናገለግልም እንደሚገደው ለማሳየት።***

*የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በእሳት ስለሚገለጥ እሳቱ የእያንዳንዱን ሰው ሥራ ምንነት ይፈትናል፡፡ ማንም የገነባው ሥራ ቢጸናለት ሽልማቱን ይቀበላል…›› 1ቆሮ 3፡13-14*

1. *1ኛ ቆሮ 3፡10-15 በማንበብ ስለ መሰረት የሚናገራቸውን ሀሳቦች በሙሉ በመዘርዘር ተናገር፡፡*
2. ***መሰረት መስርቻለሁ ብሎ ሲናገር ምን ማለቱ ነው? "እንደ ብልሃተኛ አናጺ አለቃ" የሚለው አባባል ስለመሰረቱ የሚነግረን** ነገርስ ምንድነው?*
3. *ሐዋርያው በዚህ ክፍል አንባቢዎቹን እያስጠነቀቀ ያለው ዋነኛ ነገር ምንድነው?*
4. *ጸሐፊው ማስጠንቀቂያውን የሚሰጠው ለማን ነው? ለምንድነው **እንዲህ ያለውን ጥብቅ ማስጠንቀቂያ መስጠት ያስፈለገው?***
5. ***በዚህ መሠረት ላይ ማነጽ የሚቻልባቸው** በክፍሉ ውስጥ የተዘረዘሩትን ነገሮች ተናገር፡፡*
6. ***ወርቅ፣** ብርና **የከበረ ድንጋይ ከምድር በታች የሚገኙና** ለሰው በቀላሉ የማይታዩ **የማይታዩ ሲሆኑ፤ እንጨት፥ ሳርና አገዳ ግን ከምድር በላይ ሆነው** በግላጭ **የሚታዩ** ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር አገልግሎትን በተመለከተ ምን እንማራለን? እነዚህን የህንጻ መሳሪያዎች ሌላ ሊነጻጸሩ በሚቻሉበት መንገድ አነጻጽራቸው፡፡*
7. ***የእያንዳንዱ ሥራ የሚገለጠው መቼና እንዴት ነው ይላል ክፍሉ?** በጥራት ማከናወን ጥቅም አለው ወይ? አዎን ካልክ ምን?*
8. *አገልግሎት ሽልማት ወይም ኪሳራ ባይኖረው አሁን ከምናገለግለው በተለየ መንገድ የምናገለግል ይመስልሃል ወይ? ሽልማት ወይም ኪሳራ መኖሩ ዛሬ ለአገልግሎታችን ምን ያህል የሚያነቃቃ ሆኖ ታየዋለህ?*
9. ***አንተስ የአገልግሎት ሽልማትና ኪሳራ እንዳለ** መረዳትህ **ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት ምን ያህል** አበረታትቶሃል? ከዚህ ትምህርት ወደፊት ላለው አገልግሎትህ ምን የተማርከው ነገር እንዳለ ለወገኖች አካፍል፡፡*